እርሱ ዘንድ ስሜ ተወስቶ በኔ ላይ ሶላት ያላወረደ ሰው አፍንጫው በአፈር ትታሽ፤ ረመዷንን አግኝቶ ከዚያም ከመማሩ በፊት የወጣበት ሰው አፍንጫው በአፈር ትታሽ፤ ወላጆቹን እርጅና ላይ አግኝቶ ጀነት ያላስገቡት ሰው አፍንጫው በአፈር ትታሽ።

ከአቡ ሁረይራ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "እርሱ ዘንድ ስሜ ተወስቶ በኔ ላይ ሶላት ያላወረደ ሰው አፍንጫው በአፈር ትታሽ፤
ረመዷንን አግኝቶ ከዚያም ከመማሩ በፊት የወጣበት ሰው አፍንጫው በአፈር ትታሽ፤ ወላጆቹን እርጅና ላይ አግኝቶ ጀነት ያላስገቡት ሰው አፍንጫው በአፈር ትታሽ።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሶስት አይነት ሰዎችን በውርደትና ክስረት አፍንጫቸው በአፈር እንዲታሽ ረገሟቸው: የመጀመሪያው: ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እርሱ ዘንድ ተወስተው በርሳቸው ላይ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም ወይም እርሱን የመሰለ ውዳሴ በማለት በርሳቸው ላይ ሶላት ያላወረደ ሰው ነው። ሁለተኛው: የረመዷንን ወር አግኝቶ ከዚያም አምልኮን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ምክንያት ከመማሩ በፊት ወሩ የተጠናቀቀበት ሰው ነው። ሶስተኛው: በእርጅና ወቅት ወላጆቹን አግኝቶ የነርሱን ሐቅ ባለመወጣቱና ሐቃቸውን በማጓደሉ ምክንያት ጀነት ለመግባቱ ሰበብ ያልሆኑለት ሰው ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/6014